የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሃያ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፩
አዲስ አበባ ጥቅምት ፳፪ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

23rd Year No. 1
ADDIS ABABA, 1st November, 2016

<ins>ማውጫ</ins>

**CONTENT**

አዋጅ ቁጥር ፱፻፹፬/፪ሺ፱ ዓ.ም

የሕዝብን ሰላምና ፀጥታ ለማስጠበቅ በሚኒስትሮች ምክር ቤት የታወጀውን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር ፩/፪ሺ፱ ለማፀደቅ የወጣ አዋጅ……………………ገጽ ፱ሺ፫፻፷፱

Proclamation No. 984/2016

State of Emergency for the Maintenance of Public Peace and Security Council of Ministers Proclamation No.1/2016 Ratification Proclamation.......................................page 9369

**አዋጅ ቁጥር ፱፻፹፬/፪ሺ፱**

**<ins>የሕዝብን ሠላምና ፀጥታ ለማስጠበቅ በሚኒስትሮች ምክር ቤት የወጣውን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር ፩/፪ሺ፱ ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ</ins>**

የሕዝብን ሠላምና ፀጥታ ለማስጠበቅ በሚኒስትሮች ምክር ቤት መስከረም ፳፰ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር ፩/፪ሺ፱ የታወጀ በመሆኑ፤

ይህንኑ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥቅምት ፲ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ የመረመረውና በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፺፫(፫) መሠረት ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፺፫(፫) እና ፶፭(፰) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**PROCLAMATION No.984/2016**

**<ins>A PROCLAMATION TO RATIFY THE COUNCIL OF MINISTERS PROCLAMATION NO. 1/2016 ON STATE OF EMERGENCY FOR THE MAINTENANCE OF PUBLIC PEACE AND SECURITY</ins>**

**WHEREAS**, the Council of Ministers has approved on 8th day of October 2016 a State of Emergency Proclamation for the Maintenance of Public Peace and Security No.1/2016;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has approved the State of Emergency Proclamation at its session held on the 20th day of October 2016 pursuant to Article 93 (3) of the Constitution;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 93(3) and 55(8) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

**፩.<u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "የሕዝብን ሰላምና ፀጥታ ለማስጠበቅ በሚኒስትሮች ምክር ቤት የታወጀውን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር ፩/፪ሺ፱ ለማፀደቅ የወጣ አዋጅ ቁጥር ፱፻፹፬/፪ሺ፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

**፪.<u>የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን ስለማፅደቅ</u>**

መስከረም ፳፰ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም በሚኒስትሮች ምክር ቤት የሕዝብን ሠላምና ፀጥታ ለማስጠበቅ የታወጀው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር ፩/፪ሺ፱ በኢትዮጵያ በዚህ አዋጅ ፀድቋል::

**፫.<u>የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አፈፃፀም መርማሪ ቦርድ</u>**

፩/ የሕዝብን ሰላምና ፀጥታ ለማስጠበቅ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በወጣው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ቁጥር ፩/፪ሺ፱ የተመለከተው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አፈፃፀም መርማሪ ቦርድ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤ መርማሪ ቦርዱ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ ፺፫(፭) እና (፮) እና በአዋጁ አንቀጽ ፰ እና ፱ የተመለከተው ሥልጣንና ኃላፊነቶች ይኖሩታል።

፪/ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰባት አባላት ያሉት የመርማሪ ቦርድ ይሰይማል::

**፬.<u>የቦርዱ ሰብሳቢ ስልጣንና ተግባር</u>**

የቦርዱ ሰብሳቢ፡-

፩/ ቦርዱን ይመራል፣

፪/ አጠቃላይ የስራ እንቅስቃሴውን በበላይነት ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፣

፫/ ለቦርዱ ሥራ አስፈላጊ የሆኑ ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞችን ይመድባል፣

፬/ ቦርዱን በመወከል ከሌሎች አካላት ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

**1. <u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the "State of Emergency for the Maintenance of Public Peace and Security Council of Ministers Proclamation No.1/2016 Ratification Proclamation No. 984/2016".

**2. <u>Ratification of the Proclamation</u>**

The State of Emergency Proclamation for the Maintenance of Public Peace and Security approved by Council of Ministers on 8th of day October of 2016 by Proclamation No.1/2016 is hereby ratified.

**3. <u>State of Emergency Inquiry Board</u>**

1/ The State of Emergency Inquiry Board stated under the State of Emergency Proclamation for the Maintenance of Public Peace and Security No. 1/2016 is hereby established and shall have the power and duties provided under Article 93(5) and (6) of the Constitution and Article 8 and 9 of same Proclamation.

2/ The House of Peoples'Representatives shall assign a seven member Board of Inquiry.

**3. <u>Duties and Responsibilities of the Board Chairperson</u>**

The Chairperson shall

1/ lead the Board;

2/ follow and supervise the general activities of the Board;

3/ appoint the necessary support staff of the Board;

4/ represent the Board in its dealings with other parties.

**፬.<u>የቦርዱ ምክትል ሰብሳቢ ስልጣንና ተግባር</u>**

የቦርዱ ምክትል ሰብሳቢ ፡-

፩/ ሰብሳቢው በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል፤

፪/ በቦርዱና በሰብሳቢው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

**፮.<u>የቦርዱ የስራ ቦታ</u>**

የቦርዱ ዋና ጽሕፈት ቤት አዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን በሌሎች ቦታዎች ሊከፍት ይችላል።

**፯. <u>በጀትና የሰው ሃይል</u>**

ቦርዱ ለሥራው አስፈላጊ የሆነ የሰው ሀይል፤ በጀትና ጽህፈት ቤት በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይሟሉለታል።

**፰.<u>የቦርዱ ምልዐተ ጉባኤና ውሳኔ አሠጣጥ</u>**

፩/ ከቦርዱ አባላት ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል።

፪/ የቦርዱ ውሳኔ በስብሰባው በተገኙት አባላት በአብላጫ ድምፅ ይወሰናል።

፫/ ድምፅ እኩል በእኩል ከሆነ ሰብሳቢው ያለበት ወገን የቦርዱ ውሳኔ ይሆናል ።

**፱.<u>ስለ ሪፖርት አቀራረብ</u>**

ቦርዱ ሥራውን አስመልክቶ በየጊዜው ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሪፖርት ያቀርባል።

**፲.<u>የመተባበር ግዴታ</u>**

ማንኛውም አካል ወይም ግለሰብ ቦርዱ ለሚያከናውናቸው ተግባራት የመተባበር ግዴታ አለበት ።

**፲፩.<u>መመሪያ ስለማውጣት</u>**

ቦርዱ አስፈላጊ ማስረጃና መረጃ ለመሰብሰብ፣ ምርመራ ለማካሄድ፣ ስለ ስብሰባ ስነስርዓቱ እንዲሁም ተግባር እና ሃላፊነቱን በሚገባ እንዲወጣ ለማስቻል የሚረዱ መመሪያዎችን ያወጣል።

**4. <u>Duties and Responsibilities of the Board Deputy Chairperson</u>**

The Deputy Chairperson of the Board shall

1/ represent the chairperson in his absence;

2/perform other activities assigned to him by theChairperson and the Board;

**6. <u>Head Office</u>**

The head office of the Board shall be in Addis Ababa, provided that it may have branch offices elsewhere as necessary.

**7. <u>Budget and Support Staff</u>**

The necessary support staff, budget and office of the Board shall be allocated by the House of Peoples' Representatives.

**8. <u>Quorum and Decision Making</u>**

1/ The presence of the more than half of the members of the Board shall constitute quorum.

2/ Decisions of the Board shall be passed by majority vote.

3/ in case of a tie the Chairperson shall have a casting vote.

**9. <u>Reporting</u>**

The Board shall present report from time to time to the House of Peoples' Representatives regarding its work performance.

**10. <u>Duty to Cooperate</u>**

Any body or individual shall have the duty to cooperate in the works of the Board.

**11. <u>Power to Issue Directive</u>**

The Board may issue directives on information and evidence gathering, conducting investigation, meeting procedure and other matters necessary for discharging its responsibilities.

**፲፪.<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

**ይህ አዋጅ ከመስከረም ፳፰ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም ጀምሮ ለስድስት ወራት የፀና ይሆናል፡፡**

**12. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force as of the 8th day of October 2016 and remain in effect for six months.

**አዲስ አበባ ጥቅምት ፳፪ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**Done at Addis Ababa, this 1st day of November, 2016**

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**